የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 32
ADDIS ABABA, 10th July, 2024


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፮/፪ሺ፲፮

ለኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና ተግባራት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከአለም ዐቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ…………..ገጽ ፲፭ሺ፮፻፲፫


## Content


Proclamation No. 1316/2024

International Development Association Loan Agreement for financing Ethiopia Education and Skills for Employability Project Ratification Proclamation ………..…Page 15613


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፮/ ፪ሺ፲፮

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ለኢትዮጵያ ትምህርትና ሥልጠና ተግባራት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ፩፻፶ ሚሊዮን ፬፻ሺ ኤስ.ዲ.አር. (አንድ መቶ ሃምሳ ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር.) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ጥቅምት ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህን ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም ባካሄደዉ ፲፯ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀዉ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1316/2024

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION</u>**

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to SDR 150,400,000 (one hundred and fifty million, four hundred thousand) Special Drawing Rights for financing Ethiopia Education and Skills for Employability Project was signed in Addis Ababa on 1st day of November, 2023;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Loan Agreement at its 17th regular session, held on the 14th day of March 2024;


ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና ተግባራት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፮/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ጥቅምት ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7420-ET በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፶ ሚሊዮን ፬፻ሺ ኤስ.ዲ.አር. (አንድ መቶ ሃምሳ ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር.) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቷል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 sub-articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for financing Ethiopia Education and Skills for Employability Project Ratification Proclamation No. 1316/2024".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 7420-ET signed in Addis Ababa on 1st day of November, 2023 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to SDR 150,400,000(one hundred and fifty million, four hundred thousand SDR) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this 10th Day of July,2024**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**